# ከጊቤ አንድ ግድብ በተለቀቀው ውኃ ነዋሪዎች

***ከ61 ሜጋ ዋት በላይ የሚያመነጨው ትራንስፎርመር ተቃጥሏል***

(በውድነህ ዘነበ)

***የጊቤ አንድ የኃይል ማመንጫ ጣቢያ ካሉት ሦስት ትራንስፎርመሮች መካከል አንዱ በመቃጠሉ፡፡ ግድቡ የያዘውን የክረምት ውኃ በሙሉ አቅሙ መጠቀም ባለመቻሉ የተለቀቀው ውኃ ጎርፍ ሆኖ በአካባቢው ነዋሪዎች ላይ መፈናቀልን አስከትሏል፡፡***

***ከ20 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የሚያስወጣው አንድ ትራንስፎርመር ሙሉ በሙሉ የተቃጠለ በመሆኑ በአዲስ መተካት ይኖርበታል፡፡***

***የኢትዮጵያ መብራት ኃይል ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ምህረት ደበበ ለሪፖርተር እንደገለጹት፡፡«ትራንስፎርመሩን ለመለወጥ ለአንድ የቻይና ኩባንያ ሥራውን ሰጥተናል፡፡ እኛ ውኃ ስንለቅ ግን ለሕዝብ አሳውቀን ነው፡፡ አሁን ስለተፈጠረው ጉዳይ ግን መረጃ የለኝም፣» በማለት አስረድተዋል፡፡***

***ግልገል ጊቤ አንድ 184 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል የሚያመነጭ ሲሆን፡፡አንዱ ትራንስፎርመር በመቃጠሉ 61.3 ሜጋ ዋት ኃይል እየተመረተ አይደለም፡፡ ይህም በመሆኑ ይህንን ኃይል ሊያመርት ይችል የነበረው የውኃ መጠን ከግድብ ባለመውጣቱና የአካበቢው የክረምት ዝናብ ከፍተኛ በመሆኑ ከአቅም በላይ ወደ ግድቡ ውኃ ገብቷል፡፡***

***ግድቡን ለማስተንፈስ ኮርፖሬሽኑ ውኃ የለቀቀ ሲሆን፡፡የተለቀቀው ውኃ ከመጠን በላይ በመሆኑ የአካባቢው ነዋሪዎችን በዚህ የእርሻ ወቅት ከማፈናቀሉም በተጨማሪ፡፡በእርሻ መሬቶች ላይ ጉዳት ማድረሱን ከሥፍራው የደረሰን መረጃ ያመለክታል፡፡***

***ባለሙያዎች እንደሚገልጹት፡፡ትራንስፎርመሩ በአስቸኳይ መለወጥ ሲገባው እስካሁን ምንም ዓይነት ዕርምጃ ባለመወሰዱ ተጓቷል፡፡ በቶሎ መለወጥ ባለመቻሉም መገኘት ያለበት የኤሌክትሪክ ኃይል እንዲባክን ሆኗል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በአካባቢው አርሶ አደሮች ላይ ጉዳት አይፈጠርም ነበር በማለት የኮርፖሬሽኑን አሠራር ይተቻሉ፡፡***

***በአሁኑ ወቅት ትራንስፎርመሩን ለመለወጥ የዲዛይንና የግዥ ሥራዎች እየተካሄዱ ሲሆን፡፡ ለተቃጠለው ትራንስፎርመር ኢንሹራንስ የሚሰጠው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የሚፈለገውን ወጪ እንዲሸፍን ውይይቶች እየተካሄዱ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡***

***ግልገል ጊቤ አንድ በሙሉ አቅሙ ማምረት ካለመቻሉም በላይ፡፡ግልገል ጊቤ ሁለት የውስጥ ለውስጥ ዋሻ በመደርመሱ ምክንያት በጥገና ላይ ይገኛል፡፡ እነዚህ ሁለት የጊቤ ፕሮጀክቶች ሥራዎች የተካሄዱት በጣሊያኑ ሳሊኒ ኮንስትራክሽን ሲሆን፡፡ሳሊኒ በድጋሚ ግልገል ጊቤ ሦስት የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክትን ለመገንባት ስምምነት ነበረው፡፡ ይሁንና ይገኛል የተባለው ገንዘብ ከታሰበው አበዳሪ ባለመገኘቱ የፕሮጀክቱ ዋና ዋና ግንባታዎች ወደ ቻይናው ኩባንያ ዳንግ ፋንግ ዞሯል፡፡***

***በአሁኑ ወቅት ሳሊኒ እየገነባ የሚገኘው የፕሮጀክቱን የሲቪል ወርክ ግንባታ ብቻ ነው፡፡***